በሶስት የአሜሪካ ፕሬዝደንቶች የተገመገመ የአለማችን ብቸኛ መጽሐፍ!!!

# THINK AND GROW RICH

# አስበህ ሀብታም ሁን!

2ተኛ ዕትም



የትም ኑር፣ ማንም ሁን፣ ከየትም ተነሳ... የምትፈልገውን ሃብት፣ ገንዘብ፣ እውቀት፣ ስልጣን፣ ዝና፣ ክብር... ማንኛውንም ነገር ታገኘዋለህ!!

ናፖሊዮን ሂል

ትርጉም፡ ውድሰው ደግዋለ

በሶስት የአሜሪካ ፕሬዝደንቶች የተገመገመ የአለማችን ብቸኛ መጽሐፍ!!!

# THINK AND GROW RICH

# አስበህ ሀብታም ሁን!



2ተኛ ዕትም

የትም ኑር፣ ማንም ሁን፣ ከየትም ተነሳ... የምትፈልገውን ሃብት፣ ገንዘብ፣ እውቀት፣ ስልጣን፣ ዝና፣ ክብር... ማንኛውንም ነገር ታገኛዋለህ!!

ናፖሊዮን ሂል

ትርጉም፡ ውድሰው ደግዋለ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
© All Rights Reserved

© መብቱ ሙሉ በሙሉ የአሳታሚው ነው፡፡

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ 2012 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም ሰኔ 2013 ዓ.ም

ቡክ ላንድ አሳታሚና አከፋፋይ፡-
+251 -922-74-02-02
+251- 930-08-33-08

ስለ መጽሐፉ አስተያየትና ጥያቄዎች ካለዎት
woodddeg@gmail.com

# እነሆ የሀብት ስጦታ

ለ-----------------------------------

ይህ **አስበህ ሀብታም ሁን** የተሰኘው መጽሐፍ መመለሺያ አልባ በሆነው የሕይወት መንገድ ላይ እንደመልካም መካሪ ሆኖ እንዲመራህ/ሽ እና አስበህ/ሽ ሀብታም እንድትሆን/ኚ በመመኘት ተበረከተ።

---------------------------

# ለደራሲው የተሰጡ አስተያየቶች ,

የተከበሩ ዶ/ር ሂል፡-

አሁን የስኬት ሕግ መጽሐፍዎትን አንብቤ ለመጨረስ ስለቻልኩ ይህን ፍልስፍና በማዘጋጀት ስላደረጉት አስደናቂ ሥራ አድናቆቴን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ ትምህርትዎ የተመሰረተባቸውን አሥራ ሰባት መርሆች የሀገሪቱ እያንዳንዱ ፖለቲከኛ ቢያውቃቸውና ቢተገብራቸው ጠቃሚ ይሆናል፡፡ መጽሐፍዎ በየትኛውም የሕይወት ዘርፍ ላለ ማንኛውም መሪ ማወቅ ያለበትን እጅግ ጠቃሚ መረጃ ይዟል፡፡ በዚህ አስደናቂ የተፈጥሮ "እውቀት ፍልስፍና" ትምህርት ዝግጅትዎ ወቅት የተወሰነ ድጋፍ ለማድረግ ዕድሉን በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ፡፡

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት**

(የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት

እና

ጠቅላይ ፍ/ቤት ዋና ዳኛ)

**የ5 ዶላር ከ10 ሳንቲም መደብሮች ንጉሥ፡-**

የስኬት ሕግ ፍልስፍናን አስራ ሰባቱን መርሆች በመተግበር እጅግ በርካታ ውጤታማ መደብሮችን ለመስራት ችለናል፡፡ የውልወርዝ ሕንፃ የእነዚህ መርሆች የትክክለኛነት መገለጫ ሀውልት መሆኑን ስናገር እውነት አጋኖ ማቅረብ እንዳልሆነ አምናለሁ፡፡

**ኤ. ደብሊው. ውልወርዝ፡-**

**የትልቅ መርከብ ባለፀጋ፡-**

የስኬት ህግዎትን ስላነበብኩ በጣም እድለኛ እንደሆንኩ አስባለሁ:: ይህን ትምህርት ከሃምሳ አመት በፊት ባገኘው ኖሮ፥ ያገኘሁትን ሁሉ በግማሽ ባነሰ ጊዜ ውስጥ አደርገው እንደነበር አስባለሁ:: አለም እንደሚያውቅዎት እና እንደሚያደንቅዎት ከልብ አምናለሁ::

**ሮበርት ደላር**

**ታዋቂው አሜሪካዊ የሰራተኞች መብት ታጋይ፡-**

የስኬት ህግ ፍልስፍናን ማወቅ ውድቀትን ከሚከላከል የዋስትና ውል ጋር እኩል ነው::

**ሳሙኤል ጉምፐርስ**

**የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት፡-**

ስለ ጽናትዎ አመሰግንዎታለሁ:: ያን ያህል ብዙ ጊዜ ሰጥቶ የሚሰራ ሰው… በእርግጥም ለሌሎች ብዙ ጥቅም ያላቸው ግኝቶች ያገኛል:: በትክክል በገለጡት "የላዕላይ አእምሮ" መርህ ትርጓሜዎ እጅግ በጣም ተደስቻለሁ::

**ውድሮው ዊልሰን**

**ነጋዴው ልዑል፡-**

የእርስዎ አሥራ ሰባቱ የስኬት መርሆች ትክክል እንደሆኑ አውቃለሁ፤ ምክንያቱም ከሰላሳ አመታት በላይ በስራዬ እየተገበርኳቸው ነው::

**ጆን ዋናሜከር**

**የሀገሪቱ ታዋቂ የቢዝነስ መሪ፡-**

የደረስኩበትና ያገኘሁት ማንኛውም ስኬት፥ ሙሉ በሙሉ የአስራ ሰባቱን የስኬት ሕግ መሰረታዊ መርሆች በመተግበር እንደሆነ አምናለሁ። የመጀመሪያው ተማሪዎ በመሆኔ ክብር ይሰማኛል።

**ዊሊያም ሪግሌይ**

**የዓለም እጅግ ትልቁ የካሜራ አምራች፡-**

በስኬት ሕግ አለምን እየቀየሯት እንደሆነ አውቃለሁ። የዚህን ስልጠና የገንዘብ ዋጋ ለማስቀመጥ አላስብም። ምክንያቱም ለተማሪው በገንዘብ ብቻ የማይተመኑ እጅግ በርካታ ስጦታዎችን ይሰጡታልና።

**ጆርጅ ኢስትማን**

**የዓለም እጅግ ታላቁ የፈጠራ ባለቤት፡-**

የስኬት ሕግን ዋናውን ረቂቅ ጽሁፍ በመላክ ስለ ሰጡኝ ምስጋና አድናቆቴን እንድገልፅ ይፍቀዱልኝ። በዝግጅቱ ብዙ ጊዜ እና ጉልበት እንዳሳለፉ እረዳለሁ። ፍልስፍናዎ ትክክል ነው። በስራው ለረጅም አመታት ስለደከሙ ሊመሰገኑ ይገባል። ተማሪዎችዎ በስራዎችዎ በብዙ ይደሰታሉ።

**ቶማስ ኤድሰን**

**የዓለም ዝነኛው ሳይንቲስት፡-**

የእርስዎ እና የእኔ ስራ በጣም ይመሳሰላሉ። እኔ ይበልጥ ትክክለኛ የዕፅዋት ዝርያዎችን ለመፍጠር የተፈጥሮ ህጎችን እያገዝኩ ነው። እርስዎ ደግሞ በስኬት ይበልጥ ትክክለኛ የሆኑ አሳቢ ሰዎችን ለመፍጠር እነዚህን ተመሳሳይ ህጎች እየተጠቀሙ ነው።

**ሉተር ቡርባንክ**

የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት፡-

በእርግጥ የጠየቅከውን መረጃ እሰጥሃለሁ። ይህ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ደስታም እንደሆነ አስባለሁ። የውድቀት ወይም የስኬት ምክንያቶችን ለማወቅ ጊዜም፣ ፍላጎትም ለሌላቸው ሰዎች ተወካይ በመሆን እየደከምክ ነው።

**ቴዎድር ሩዝቬልት**

ይህ ልብወለድ አይደለም። እጅግ ስኬታማ ከሆኑ ከብዙ መቶ አሜሪካኖች ልምድ በቀጥታ የመጣ ማንኛውንም ስኬት የሚያስተምር የመማሪያ መጽሐፍ ነው። ሊጠና፣ ሊዋሀድ እና ሊሰርፅ ይገባል። በአንድ ምሽት ከአንድ ምዕራፍ በላይ መነበብ የለበትም። አንባቢው በጣም የሚስቡትን ዓረፍተ ነገሮች ሊያሰምር ይገባዋል። እውነተኛ ተማሪ ይህን መጽሐፍ ማንበብ ብቻ ሳይሆን፣ የያዛቸውን ሀሳቦች በማስረፅ የራሱ ያደርጋቸዋል። ይህ መጽሐፍ በሁሉም የሁለተኛና የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሊሰጥ ይገባል። ማንኛውም ተማሪ የዚህን ፈተና በብቃት ካላለፈ ወደሚቀጥለው ክፍል እንዲሸጋገር ሊፈቀድለት አይገባም። ይህ ፍልስፍና በት/ቤቶች የሚሰጡትን ትምህርቶች የሚተካ ሳይሆን፣ አንድ ሰው ያገኘውን እውቀት እንዲያደራጅና እንዲተገብር እና ጊዜን ባለማባከን ወደ ጠቃሚ አገልግሎትና ከፍተኛ ክፍያ እንዲቀይረው የሚያስችል ነው።

**ዶ/ር ሚለር ሩሴ ሁቺሰን**

(የሀገሪቱ የታወቀ አማካሪ ኢንጅነር እና

የቶማስ ኤድሰን የረጅም ጊዜ ረዳት)

ገጽ

## ማውጫ


................................13

የደራሲው አስተያየት ................................19

ምዕራፍ ፩. ሀሳቦች ቁሶች ናቸው ................................

### ከቶማስ ኤድስን ጋር ሽርክና የሚገባበትን መንገድ "ያሰበው" ሰው

ተመራማሪው እና ከርታታው፣ የዕድል ስውር መደበቂያዎች፣ ከወርቅ ክምር ሶስት ጫማ ሲቀር፣ ሰዎች አይቻልም ስላሉ አላቆምም፣ የፅናት የሃምሳ ሣንቲም ትምህርት፣ የህፃኗ እንግዳ ኃይል፣ አንድ ትክክለኛ ሀሳብ ያስፈልግሃል፣ "ሊሆን የማይችለው" ፎርድ ቪ-8 ሞተር፣ ለምንስ የእጣ ፈንታህ ጌታ ሆንክ፣ ፍፃሜህን የሚወስኑ መርሆች፣

ምዕራፍ ፪. ፍላጎት ................................36

### የሁሉም ስኬት መነሻ ነጥብ

*ወደኋላ ላለመመለስ የወሰነው ሰው፣ ወደ ብዙ ሀብት የሚገፋፋህ መነሳሳት፣ ፍላጎትን ወደ ወርቅ የመቀየር ስድስት መንገዶች፣ ራስህን ሚሊነየር አድርገህ መቁጠር ትችላለህ?፣ የትልቅ ህልሞች ኃይል፣ ህልሞች እንዴት ከማኮብኮቢያው ሜዳ እንደሚነሱ፣ ፍላጎት ነበራዊ አለምን ያሞኛል፣ ሕይወትን የቀየረ "አጋጣሚ" በስድስት ሳንቲሞች አዲስ አለም አግኝቷል፣ መስማት የተሳነው ብላቴና ሰማ፣ ተአምራት የሚሰራ ሀሳብ፣ "የአእምሮ ኬሚስትሪ" ተአምር ይሰራል*

ምዕራፍ ፫. እምነት ................................54

### ፍላጎትን በዓይነ-ህሊና ማየት እና በማግኘት ማመን

እምነትን ማሳደግ፣ ማንም ለመጥፎ ዕድል አልተፈጠረም፣ እምነት በግለ-አስተያየት ሊሰርፅ የሚችል የአእምሮ ገፅታ ነው፣ የግለ-አስተያየት ተአምር፣ በራስ የመተማመን ቀመር፣ የአሉታዊ አስተሳሰብ ጥፋት፣ እንዴት ያለ ተሰጥኦ ከአእምሮህ ውስጥ ተኝቷል?፣ ሀሳብ

ሀብት እንዴት እንደፈጠረ፣ ሀብት ከሀሳብ ይጀምራል።

ምዕራፍ ፬. ግለ-አስተያየት ........................................ 74

ጥልቁን አእምሮ የማሳመኛ መንገድ

ገንዘብ በእጆችህ ላይ እይ እና እመን፣ የተመሰጠ ኃይሎችህን ማጠንከር፣ ድብቁ አእምሮን ለማነሳሳት ስድስት ደረጃዎች፣ የአእምሮ ኃይል ምሥጢር።

ምዕራፍ ፭. ጥልቅ እውቀት ........................................ 82

ግላዊ ልምዶች ወይም እይታዎች

እጅግ ብዙ ሀብት የፈጠረው "መሀይሙ" ሰው፣ የሚያስፈልግህን እውቀት ሁሉ ማግኘት ትችላለህ፣ እውቀት መግዛት ማወቅ ይከፍላል፣ ከገቢ ሰብሳቢ ወኪል የተገኘ ትምህርት፣ ወደ ጥልቅ እውቀት የሚወሰደው መንገድ፣ ስኬታማው ቀላል ሀሳብ፣ ጥሩ ስራ ለማግኘት የተፈተሸ ዕቅድ፣ ከታች መጀመር የለብህም፣ ለአንተ ያለመርካት ስራ አድርግ፣ አጋሮችህ እጅግ ውድ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ሀሳቦችህን በጥልቅ እውቀት ላይ መስርታቸው።

ምዕራፍ ፮. ምናብ ........................................ 98

የአእምሮ መስሪያ ክፍል

የምናብ ሁለት ገፅታዎች፣ ምናብህን አለማምደው፣ ወደ ሀብት የሚመሩ ህጎች፣ በምናብ ተጨባጭ ጥቅም ማግኘት፣ የተከተበባት ማንቆርቆሪያ፣ አንድ ሚሊዮን ዶላር ቢኖረኝ ምን አደርጋለሁ፣ ሀሳቦችን ወደ ገንዘብ መለወጥ።

ምዕራፍ ፯. የተደራጀ ዕቅድ ........................................ 111

ፍላጎት ወደ ተግባር የመጠንከር ሂደት

የመጀመሪያ ዕቅድህ ባይሳካ ሌላኛውን ሞክር፣ የግል አገልግሎቶች

ሸያጭ ዕቅድ፣ ብዙ መረዎች እንደ ተከታዮች ይጀምራሉ፣ ዋና የመሪነት ብቃቶች፣ አስር ዋና የመሪነት የውድቀት ምክንያቶች፣ "አዲስ መሪነት" የሚፈለግባቸው የተወሰኑ ውጤታማ ዘርፎች፣ ለአንድ የስራ ቦታ መቼ እና እንዴት ማመልከት፣ በተፃፈ አጭር መግለጫ የሚቀርብ መረጃ፣ የምትፈልገው ትክክለኛ የኃላፊነት ቦታ ይገኛል፣ አገልግሎቶችን የመገበያያ አዲሱ ዘዴ፣ የአገልግሎትህ የ"ጥመመ" ልኬት ስንት ነው፣ የአገልግሎቶችህ የገንዘብ ዋጋ፣ ሰላሳ አንድ ዋና የውድቀት ምክንያቶች፣ የራስህን ዋጋ ታውቃለህ፣ ስለ ራስህ ጥናት አድርግ፣ የራስ ጥናት ግለ-ትንተና መጠይቅ፣ አንድ ሰው ብዙ ሀብቶች ለማፍራት የት እና እንዴት እንደሚያገኝ፣ እነዚህን በረከቶች የሰጠው "ተአምር"፣ ካፒታል የሕይወቶቻችን የማዕዘን ድንጋይ... ዕድሎችህ...

ምዕራፍ ፰. ውሳኔ ....................................................................158

## የማዘግየት ጌታ

የራስህን ውሳኔዎች የምትወስንባቸው ነጥቦች... የነፃነት ወይም የሞት ውሳኔ... ከስቅለት ያመለጡ ሃምሳ ስድስት ሰዎች... የላዕላይ አእምሮ ጥምረት... ታሪክን የቀየረ ውሳኔ... ወረቀት ላይ ከሰፈሩት ሁሉ ትልቁ ታሪካዊ ውሳኔ... ምን እንደምትፈልግ እወቅ ከዚያ ታገኘዋለህ...

ምዕራፍ ፱. ፅናት ....................................................................171

## እምነት ለማስረፅ አስፈላጊ የሆነ የማያቋርጥ ጥረት

የጽናት መለኪያህ... "ገንዘብ ተኮር" ወይስ "ድህነት ተኮር" ነህ?... ከአእምሮ ፍዘት መንቃት... ውድቀቶችህን አሸንፍ... ፅኑ እንድትሆን ራስህን ማሰልጠን ትችላለህ... የራስን 'የፅናት መመዘኛ" ውሰድ... ትችት ከፈራህ... ዕድሎች ይቀጣጠላሉ... ፅናትን ማምጣት... ችግሮችን መወጣት...

ምዕራፍ ፲. የላዕላይ አእምሮ ኃይል ....................................................................188

## አበረታቹ ኃይል

በላዕላይ አእምሮ በኩል ኃይል ማግኘት
...የአእምሮህን ኃይል መጨመር...የአዎንታዊ
ስሜቶች ኃይል...

ምዕራፍ ፲፩. የወሲብ ቅየራ ጥበብ ..........196

ስኬት በጣም ከደጉ የወሲብ ባህርያት ጋር ያለው ዝምድና... አስሩ የአእምሮ አነቃቂ ስሜቶች... "ጂኒየስ" በስድስተኛው ስሜት ያድጋል... ሀሳቦች ከየት ይመጣሉ... የፈጠራ ችሎታን ማሳደግ... አንድ ተመራማሪ አስደናቂ ሀሳቦቹን እንዴት እንዳገኘ... ጂኒየሶች የተጠቀሟቸው ዘዴዎች ለአንተም አሉ... የወሲብ ቀስቃሽ ኃይል... ብዙ ሰዎች ከአርባ አመት በፊት ለምን ስኬታማ እንደማይሆኑ... ከሁሉም የአእምሮ ቀስቃሽ ስሜቶች እጅግ ከፍተኛው... የግለዊ ስበት አቅም... ስለ ወሲብ የሰብዕና ጉዳት የተሳሳቱ አስተሳሰቦች... ከአርባ በኋላ ያሉ ውጤታማ አመታት... የስሜቶችህን ኃይል ተጠቀም... እውነተኛ ፍቅር ያለው ሙሉ በሙሉ አይጠፋም... ሚስት የምትለውጥበት ወይም የምታጠፋበት ምክንያቶች... ያለ ሴት ሀብት ከንቱ ነው...

ምዕራፍ ፲፪. ድብቁ አእምሮ ..........220

አገናኙ መስመር

ድብቁ አእምሮህን ለፈጠራዊ ኃይል ማሳደግ... አዎንታዊ
ስሜቶች ይሰሩልሀ... የውጤታማ ጸሎት ምሥጢር...

ምዕራፍ ፲፫. አእምሮ ..........228

የሀሳብ መቀበያ እና ማሰራጫ ጣቢያ

እጅግ ከፍተኛ ኃይሎች አይታዩም፣ የአእምሮ አስደናቂ ተፈጥሮ፣
አእምሮዎችን በአንድ ላይ ማጣመር

ምዕራፍ ፲፬. ስድስተኛው ስሜት ..........236

ወደ ጥበብ ቤት የሚወስደው በር

የስድስተኛው ስሜት ተአምራት... ታላላቅ ሰዎች ሕይወትህን
ይቅረፁት... አስገራሚው የምናብ ኃይል... በግሉ አስተያየት

ማንነትን መገንባት... የመነሳሳት ምንጭን ማግኘት...
የአዝጋሚ እድገት ፅኑ ኃይል...

**ምዕራፍ ፲፫. ስድስቱ የፍርሃት መንፈሶች ........................................ 245**

*ስድስቱ መሠረታዊ ፍርሃቶች... የድህነት ፍርሃት ... እጅግ በጣም አጥፊው ፍርሃት... የድህነት ፍርሃት ምልክቶች... ገንዘብ ይናገራል... የትችት ፍርሃት... የትችት ፍርሃት ምልክቶች... የህመም ፍርሃት... የህመም ፍርሃት ምልክቶች... ፍቅር የማጣት ፍርሃት... ፍቅር የማጣት ፍርሃት ምልክቶች... የእርጅና ፍርሃት... የእርጅና ፍርሃት ምልክቶች... የሞት ፍርሃት... የሞት ፍርሃት ምልክቶች... ከንቱ ጭንቀት... የአፍራሽ አስተሳሰብ ጥፋት... የሰይጣን ባሪያ... ከአሉታዊ ተፅዕኖዎች ራስን መጠበቅ... የግለ-ትንተና ፈተና ጥያቄዎች... በአንድ ነገር ላይ ፍፁም ኃይል አለህ... የታካች ሰው "የቢሆን ኖሮ" ሃምሳ አምስት ታዋቂ ምክንያቶች።*

**ማጠቃለያ ........................................................................282**

**አስራ ሰባቱ የስኬት መርሆች**

**ስለ ደራሲው ........................................................................290**

# የደራሲው አስተያየት

በዚህ መጽሐፍ በእያንዳንዱ ምዕራፍ እኔ ለብዙ ዘመናት በጥንቃቄ ያጠናኋቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ እጅግ ሀብታም የሆኑ ሰዎች ለስኬት ያበቃቸው የገንዘብ መፍጠር ምሥጢር በሰፊው ተብራርቷል፡፡ ምስጢሩ ወደ አእምሮዬ የገባው በአንድሪው ካርነጌ አማካኝነት ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት ነበር፡፡ ስኮትላንዳዊው ብልህና ተወዳጅ አዛውንት ገና ልጅ ሳለሁ እንደነገሩ ወደ አእምሮዬ ወረወረው፡፡ ከዚያም ወንበሩ ላይ ዘና ብሎ ተቀመጠና የነገረኝ ነገር ያለውን ሙሉ ጠቀሜታ በበቂ ለመረዳት አእምሮ እንዳለኝ ለማወቅ በሚያስደስት ፈገግታ በጥንቃቄ ተመለከተኝ፡፡ ሀሳቡን እንደያዝኩት ሲያይ÷ ምስጢሩን ለዓለም እና ሕይወታቸው ከንቱ ለሚሆንባቸው ወንዶች እና ሴቶች ለመግለጥ ራሴን በማዘጋጀት ሃያ አመታት ወይም ከዚያ በላይ ለማሳለፍ ፈቃደኛ መሆኔን ጠየቀኝ፡፡ አደርገዋለሁ አልኩ፡፡ እናም በሚስተር ካርነጌ ትብብር የገባሁትን ቃል ፈፀምኩ፡፡ ይህ መጽሐፍ በሁሉም የሕይወት ጉዞዎች በሺዎች ሰዎች ተግባራዊ የሆነውን ምሥጢር ይዟል፡፡ ሰዎች እንዴት ሀብት እንደሚያገኙ ለማጥናት ጊዜ የሌላቸው ሰዎች እሱን ከፍተኛ ባለፀጋ ያደረገውን ተአምረኛ ቀመር እንዲያውቁት የሚስተር ካርነጌ ሀሳብ ነበር፡፡ እናም የቀመሩን ትክክለኛነት በወንዶች እና በሴቶች ተሞክሮ በየፊናው እንዳረጋግጥ እና እንድገልፅ ተስፋው ነበር፡፡ ቀመሩ በሁሉም የመንግስት ት/ቤቶች እና ኮሌጆች መሰጠት እንዳለበት ያምናል፡፡ ትምህርቱም በአግባቡ ከተሰጠ በት/ቤት ውስጥ የሚፈጀውን ጊዜ ከግማሽ በታች እንዲሆን ስለሚያደርገው መላውን ሥርዓተ-ትምህርት እንደሚያሳድገው ያለውን ሀሳብ ገልጿል፡፡

በእምነት ላይ ባለው ምዕራፍ ውስጥ በአንድ ወጣት የተፀነሰው እና የተተገበረው፣ በእርሱም በሚስተር ካርነጌ ቀመሩን ለሚቀበሉት ሁሉ እንደሚሰራ ያረጋገጠበትን የግዙፉን ዩ.ኤስ. ብረታ ብረት ኮርፖሬሽን

አስደናቂ ታሪክ ታነባላችሁ። ይህ የቻርለስ ኤም. ሽዋብ የምሥጢሩ ነጠላ ተግባር በገንዘብና በዕድል በሁለቱም ከፍተኛ ሀብት እንዲሰበሰብ አድርጎታል። ይህ የቀመሩ ትግበራ ምሳሌ በግምት ስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር አስገኝቷል። እነዚህ እውነታዎች÷ ሚስተር ካርነጊን ለሚያውቁ ለአብዛኞቹ በደንብ የታወቁ እውነታዎች ሲሆኑ÷ የምትፈልገው ምን እንደሆነ ካወቅክ፥ ይህን መጽሐፍ በማንበብ ስለምታገኘው ነገር ትክክለኛ ሀሳብ ይሰጡሃል። ሚስተር ካርነጊ እንዳቀደው ምስጢሩ ለግል ጥቅሞቻቸው ላዋሉት ለሺህዎች ወንዶች እና ሴቶች ተላልፏል። አኩሌቶች ብዙ ሀብት አፍርተውበታል። ሌሎች በቤታቸው ውስጥ ሰላም ለመፍጠር በትክክል ተጠቅመውበታል። አንድ ካህን በአመት ከ$75000 በላይ ገቢ ለማግኘት በጥሩ ሁኔታ ተጠቅሞበታል። የሲንሲናቲይ ልብስ ሰፊ አርሰር ናሽ ውጤት ሳያሳይ በነበረው ስራው ላይ እንደ መድኃኒት መሞከሪያ ቀመሩን ፈትሾበታል። ስራው ሕይወት ዘርቶበት ለባለቤቶቹም ብዙ ሀብት አስገኝቶላቸዋል። ምንም እንኳ ሚስተር ናሽ ቢያልፍም÷ ስራው አሁንም እያደገ ነው። ምርምሩ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ለህዝባዊ ገለፃ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ የከፈሉበት በጣም ድንቅ የሆነ ስራ ነው።

ምስጢሩ ወደ ቴክሳሱ ሰው ስታዋርት አውስቲን ዌር ተላልፏል። እሱ ለምሥጢሩ ዝግጁ ነበር። በጣም ዝግጁ ስለሆነ ሙያውን ትቶ ሕግ አጠና። እናስ ተሳካለት? ይህም ታሪክ ይነገራል። በላሳሌ ኤክስቴንሽን ዩኒቨርስቲ የማስታወቂያ ስራ አስኪያጅ ሆኜ በምሰራበት ወቅት የዩኒቨርስቲውን ፕሪዝዳንት ጂ. ጂ. ቻፕሊን ቀመሩን በትክክል ተጠቅሞ በስም ብቻ ይታወቅ የነበረውን ላስሌ ከአገሪቱ ትልቅ የኤክስቴንሽን ት/ቤቶች አንዱ ሲያደርገው ለማየት እድሉን አግኝቻለሁ።

የምገልጠው ምሥጢር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከመቶ ላላነሰ ጊዜ ተጠቅሷል። ዝግጁ ለሆኑና ለሚፈልጉት እንዲያነሱት ሳይሸፈን ሲቀርና በግልጥ ሲተው ይበልጡን የሚሰራ ስለሚመስል በቀጥታ አልተጠራም።

ለዚያም ነው ሚስተር ካርነጊ ውሱን ስሙን ሳይነግረኝ በእርጋታ በእኔ ላይ የጨመረው፡፡ ልትተገብረው ዝግጁ ከሆንክ÷ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ቢያንስ አንዴ ይህን ምሥጢር ትረዳለህ፡፡ ዝግጁ ከሆንክ እንዴት እንደምታውቀው÷ ነገር ግን ግኝቱን በራስህ መንገድ ስታደርግ የምታገኘውን ብዙ ጥቅም እንደሚያሳጣህ እንድነግርህ መብቱ እንዲኖረኝ እመኛለሁ፡፡ ተስፋ ቆርጠህ ከነበርክ÷ መልካም ማንነትህን ከውስጥህ ያጠፉብህን ችግሮች ማሸነፍ ካልቻልክ÷ ሞክረህ ካልተሳካልህ÷ በበሽታ ወይም በአካላዊ ጥቃት የአካል ጉዳተኛ ከሆንክ÷ የወንዱ ልጄ ታሪክ እና የካርነጌ ቀመር ጠቀሜታ አንተ ለምትፈልገው ምንም በሌለበት በረሃ ላይ ያለ የውሃ ምንጭ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ ይህ ምሥጢር በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት በፕሬዝዳንት ውድሮው ዊልሰን አማካኝነት በሃይለኛው ጠቅሟል፡፡ በጦርነቱ ለተዋጉት ለእያንዳንዱ ወታደር ወደ ግንባር ከመሄዱ በፊት በጥንቃቄ በስልጠናው ውስጥ በማካተት ተሰጥቷል፡፡ ፕሬዝዳንት ዊልሰን ለጦርነቱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ ዋናው ምክንያት እንደሆነም ነግረውኛል፡፡ የዚህ ምሥጢር ልዩው ነገር አንዴ ያወቁትና የተጠቀሙበት ራሳቸውን የስኬት ጣሪያ ላይ ማግኘታቸው ነው፡፡ ከተጠራጠርክ÷ በየቦታው የተጠቀሱ ምሥጢሩን የተጠቀሙትን ሰዎች ታሪክ አጥና፡፡ ራስህ ታሪካቸውን አመሳክርና እመን፡፡ ያለምንም ነገር የሚሆን አንዳች የለም፡፡

*There is no such thing as something for nothing!*

የምገልጠው ምሥጢር ምንም እንኳ ክፍያው ከእሴቱ በጣም ያነሰ ቢሆንም ያለ ክፍያ የሚገኝ ግን አይደለም፡፡ ሆን ብለው ለማይፈልጉት በምንም ያህል ዋጋ ቢሆንም አይገኝም፡፡ አይሰጥም፤ በገንዘብ አይገዛም፤ ምክንያቱም በሁለት አይነት መንገድ ብቻ ስለሚመጣ፡፡ አንደኛው አይነት አስቀድሞ ዝግጁ ለሆኑት በእጃቸው ነው፡፡ ምስጢሩ ዝግጁ ለሆኑለት በእኩል በደህና ይጠቅማል፡፡ ትምህርት ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር የለውም፡፡ እኔ ከመወለዴ ከብዙ ዓመት በፊት÷ ምሥጢሩ የቶማስ ኤ. ኤድሰን ሀብት

ሆኗል፡፡ ምንም እንኳ የሶስት ወር ብቻ ትምህርት ቢኖረውም÷ ምሥጢሩን በትክክል በመጠቀም የምድራችን መሪ ፈጣሪ ሆኗል፡፡ ምስጢሩ ወደ ቶማስ ኤድሰን የቢዝነስ አጋር ኤድዊን ሲ. ባርነስም ተላልፏል፡፡ ምሥጢሩን በትክክል በመጠቀም ምንም እንኳ በአመት $12,000 ብቻ ቢያገኝም፣ ብዙ ሀብት በማፍራት ገና ወጣት ሳለ የናጠጠ ሃብታም ለመሆን ችሏል፡፡ ሀብት ታሪኩን በመጀመሪያው ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ታገኘዋለህ፡፡ ሀብት ልትደርስበት ከምትችለው በላይ እንዳይደለ ልትረዳ ይገባሃል፡፡ አሁንም መሆን የምትፈልገውን መሆን ትችላለህ፡፡ ገንዘብ፣ ዝና፣ እውቅናና ደስታ እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት ዝግጁ እና ቆራጥ ለሆኑ ሁሉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ነገሮች እንዴት አውቃለሁ? መጽሐፉን ከመጨረስህ በፊት መልስ ልታገኝ ይገባል፡፡ ገና ከመጀመሪያው ምዕራፍ፣ አልያም ከመጨረሻው ገጽ ልታገኘው ትችላለህ፡፡ በሚስተር ካርነጌ ጥያቄ መሰረት የሃያ አመት ጥናት ተግባር ሳከናውን በመቶዎች የሚቆጠሩ ዝነኛ ሰዎችን አጥንቻለሁ፡፡ ከእነርሱ ብዙዎቹ በካርነጌ ምሥጢር እገዛ ብዙ ሀብቶቻቸውን እንደሰበሰቡ አምነዋል፡፡

ከእነዚህ ሰዎች መካከል፡-

ሄነሪ ፎርድ
ዊልያም ሪግሊይ ጁ.
አር
ጆን ዋናማከር
ጄምስ ጄ. ሂል
ጆርጅ ኤስ. ፓርከር
ኢ. ኤም ስታትለር
ሄነሪ ኤል. ዶሀርቲ
ሳይረስ ኤች. ኬ.
ከርቲስ
ጆርጅ ኢስትማን
ቻርለስ ኢም. ሽዋብ
ሃሪስ ኤፍ.
ዊልያምስ
ዶ/ር ፍራንክ
ጉንሳውለስ
ዳንኤል ዊልያርድ
ኪንግ ጊሌት
ራልፍ ኤ. ዊክስ
ዳኛ ዳንኤል ቲ.
ራይት
ጆን ዲ. ሮክፌለር
ቶማስ ኤ. ኤድስን
ፍራንክ ኤ.
ቫንደርሊፕ
ኤፍ. ደብልዩ
ውልወርዝ
ኮ/ል ሮበርት ኤ.
ዶላር ኤድዋርድ ኤ.
ፊላን ኢድዊን ሲ.
ባርንስ አርሰር ናሽ
ክላረንስ ዳሮው
ቴዎድር ሩስቬልት
ጆን ደብልዩ ዳቪስ
ኤልበርት ሁባርድ
ዊልበርት ራይት
ዊልያም ጀኒንግስ
ብርያን
ዶ/ር ዴቪድ ስታር
ጆርዳን
ጄ. ኦድጃን አርመር
አርሰር ክሪስቤን
ውድሮው ዊልሰን
ዊልያም ሀውአርድ
ታፍት
ሉተር ቡርባንክ
ኤድዋርድ ደብልዩ
ቡክ ፍራንክ ኤ.
ሙንሲይ ኤልበርት
ኤች ጋሪ
ዶ/ር አሌክሳንደር
ግርሃም ቤል
ጆን ኤች. ፓተርስን
ጁልየስ ሮስንዋልድ
ስትዋርት አውስቲን
ዊር ዶ/ር ፍራንክ
ክሬን
ጆርጅ ኤም.
አሌክሳንደር
ጄ. ጂ. ቻፕሊን
ሴናተር ጀኒንግስ
ራንዶል

እነዚህ ሰዎች በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዝነኛ አሜሪካውያን መካከል በጣም ጥቂቶች ሲሆኑ÷ በገንዘብ ወይም በሌላ ስኬቶቻቸው የካርነጌን ምሥጢር ለሚወዱ እና ተግባራዊ ለሚያደርጉ፣ የሕይወት ከፍተኛ ቦታዎች እንደሚደርሱ ያረጋግጣል። ምስጢሩን ለመጠቀም ተነሳስቶ በተሰማራበት ዘርፍ ትልቅ ስኬት ያላገኘ አንድም ሰው አላውቅም። ያለዚህ ምሥጢር ራሱን ያወቀ ወይም የትኛውንም ዓይነት ሀብት ያከማቸ አንድም ሰው አላውቅም። ከእነዚህ ሁሉ እውነታዎች በመነሳት ምሥጢሩ እንደ አንድ የእውቀት ዘርፍ ራስን ለመምራት አስፈላጊ መሆኑ ማንም ሰው "በትምህርት" ከሚያገኘው በላይ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ።

በነገራችን ላይ "ትምህርት" ምንድን ነው? ይህ በዝርዝር መልስ ተሰጥቶበታል። ዝግጁ ከሆንክ ስታነብ የሆነ ቦታ የምገልጠው ምሥጢር ከገጹ ተነስቶ ከፊትህ በግልፅ ይቆማል። በተገለጠም ጊዜ ታዋለህ! ምልክቱን በመጀመሪያውም ሆነ በመጨረሻው ምዕራፍ ስታገኘው÷ ያ ሁኔታ የሕይወትህን እጅግ አስፈላጊ አዲስ መልክ ስለሚያሳይ÷ ራሱን በሚገልጥበት ጊዜ ማንበብህን ለጊዜው አቁምና አስተውል። መጽሐፉን ስታነብ ስለ ተረት ሳይሆን ስለ እውነታዎች ስለሚያወራ÷ አላማውም ዝግጁ ለሆኑለት ሁሉ ምን ማድረግ እና እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ለሚማሩ ትልቅ ነባራዊ ሀቅ ስለሚያስተላልፍ አስተውል። ጅማሮ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ማነቃቂያም ታገኛለህ። የመጀመሪያውን ምዕራፍ ከመጀመርህ በፊት÷ የካርነጌን ምሥጢር የሚታወቅበትን ፍንጭ የሚሰጥ አንድ አጭር አስተያየት እሰጥሃለሁ። እሱም ይህ ነው፡- *ሁሉም ዓይነት ስኬት፣ ሁሉም ሀብቶች ጅማሬያቸው ከሀሳብ ነው!* ለምሥጢሩ ዝግጁ ከሆንክ÷ አስቀድመህ ግማሹን አግኝተሃል። ቀሪውን ግማሽ ደግሞ አእምሮህ በደረሰ ቅፅበት ወዲያው ታውቀዋለህ።

# አእምሮህ ሀብታም ሁን!

አሁን የስኬት ሕግ መጽሐፍዎትን አንብቤ ለመጨረስ ስለቻልኩ ይህን ፍልስፍና በማዘጋጀት ስላደረጉት አስደናቂ ሥራ አድናቆቴን ለመግለፅ እወዳለሁ። መጽሐፍዎ በየትኛውም የሕይወት ዘርፍ ላለ ማንኛውም መሪ ማወቅ ያለበትን እጅግ ጠቃሚ መረጃ ይዟል። በዚህ አስደናቂ የተፈጥሮ “እውቀት ፍልስፍና” ትምህርት ዝግጅትዎ ወቅት የተወሰነ ድጋፍ ለማድረግ ዕድሉን በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ።

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት**
**32ተኛ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ዋና ዳኛ**

በእርግጥ የጠየቅከውን መረጃ እሰጥሃለሁ። ይህ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ደስታም እንደሆነ አስባለሁ። የውድቀት ወይም የስኬት ምክንያቶችን ለማወቅ ጊዜም፣ ፍላጎትም ለሌላቸው ሰዎች ተወካይ በመሆን እየደከምክ ነው።

**ቴዎድር ሩዝቬልት**
**26ተኛ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት**

ስለ ጽናትዎ አመሰግንዎታለሁ። ያን ያህል ብዙ ጊዜ ሰጥቶ የሚሰራ ሰው... ለሌሎች ብዙ ጥቅም ያላቸው ግኝቶች በእርግጥ ያገኛል። በትክክል በገለጡት “የላዕላይ አእምሮ” መርህ ትርጓሜዎ እጅግ በጣም ተደስቻለሁ።

**ውድሮው ዊልሰን**
**28ተኛ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት**

የእርስዎ እና የእኔ ስራ በጣም ይመሳሰላሉ። እኔ ይበልጥ ትክክለኛ የዕፅዋት ዝርያዎችን ለመፍጠር የተፈጥሮ ህጎችን እያገዝኩ ነው። እርስዎ ደግሞ በስኬት ይበልጥ ትክክለኛ የሆኑ አሳቢ ሰዎችን ለመፍጠር እነዚህን ተመሳሳይ ህጎች እየተጠቀሙ ነው።

**ሉተር ቡርባንክ**
**የዓለም ዝነኛው ሳይንቲስት**

የስኬት ሕግ ፍልስፍናን አስራ ሰባቱን መርሆች ብዙዎቹን በመተግበር እጅግ በርካታ ውጤታማ መደብሮችን ለመስራት ችለናል። የውልወርዝ ሕንፃ የእነዚህ መርሆች የትክክለኛነት መገለጫ ሀውልት መሆኑን ስናገር እውነት አጋኖ ማቅረብ እንዳልሆነ አምናለሁ።

**ኤ. ደብሊው. ውልወርዝ**

የስኬት ህግዎትን ስላነበብኩ በጣም እድለኛ እንደሆንኩ አስባለሁ። ይህን ትምህርት ከሃምሳ አመት በፊት ባገኛው ኖሮ፥ ያገኘሁትን ሁሉ በግማሽ ባነሰ ጊዜ ውስጥ አደርገው እንደነበር አስባለሁ። ዓለም እንደሚያውቅዎት እና እንደሚያድቅዎት ከልብ አምናለሁ።

**ሮበርት ደላር**
**የትልቅ መርከብ ባለፀጋ**

የስኬት ሕግን ዋናውን ረቂቅ ጽሁፍ በመላክ ስለ ሰጡኝ ምስጋና አድናቆቴን እንድገልፅ ይፍቀዱልኝ። በዝግጅቱ ብዙ ጊዜ እና ጉልበት እንዳሳለፉ እረዳለሁ። ፍልስፍናዎ ትክክል ነው። በስራው ለረጅም አመታት ስለደከሙ ሊመሰገኑ ይገባል።

**ቶማስ ኤድሰን**
**የዓለም እጅግ ታላቁ የፈጠራ ባለቤት**

ራዲያን ማተሚያ ቤት 0965677051

BOOK LAND
ቡክላንድ
0922740202

EIDO ADVERT

ዋጋ 200.00 ብር
ዋጋ ሁለት መቶ ብር